# የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል

# CATERING AND TOURISM TRAINING CENTER

## ዜና መጽሔት

በኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ


በውስጥ ገጾች

- የማዕከሉ የስራ አፈጻጸም ግምገማ
- የሰልጣኞች የተግባር ስልጠና
- ወቅታዊና ሀገራዊ ጉዳዮች
- አረንጓዴ አሻራ


### መልዕክት

የተከበራችሁ የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ማህበረሰብ በሙሉ፣ የባለድርሻ አካላትና አጋር አካላት እንዲሁም የዘርፉ ባለሙያዎችና መላው ኢትዮጵያውያን እንኳን ለ2014 ዓ.ም አደረሳችሁ!

አዲሱ ዓመት የሰላም እና የስኬት እን-ዲሆን መልካም ምኞታችንን እንገልጻለን!

2014

፳፻፲፬

ዓ.ም





የማሰልጠኛ ማዕከሉ እና ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በጋራ ለመስራት በሚያስችላቸው ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት ተካሄደ።

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ጳጉሜ 04/2013 ዓ ም

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል እና ሀዋሳ ዩንቨርሲቲ በጋራ ለመስራት በሚያስችላቸው ጉዳዮች ዙሪያ የሁለቱ ተቋማት ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች ውይይት አድርገዋል።

በውይይቱ ወቅት የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት ማዕከሉ አንጋፋና በዘርፉ የካበተ ልምድ ያለው መሆኑን ገልጸው በስልጠና፣በጥናትና ምርምርና በማማከር አገልግሎት ከዩኒቨርሲቲው ጋር በቅንጅት በመስራት የሀገራችንን የቱሪዝም ዘርፍ ማሳደግ እንደሚቻል አብራርተዋል።

የአዋሳ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር አያኖ በራሶ በበኩላቸው ዩኒቨርሲቲያቸው ከማሰልጠኛ ማዕከሉ ጋር አብሮ ለመስራት ቁርጠኛ መሆኑን ገልጸው ጥሩ ልምዶችን ለመለዋወጥ ይረዳል ብለዋል።









የማሰልጠኛ ማዕከሉ ያቀረበው የደምብ ማሻሻያ ጸድቆ በተሻለ አደረጃጀት ሀገራዊ ኃላፊነቱን ሊወጣ እንደሚገባ የተከበሩ ወ/ሮ አበባ ዮሴፍ ገለጹ።

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ነሐሴ 15/2013 ዓ.ም

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሴቶች፣ ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ አበባ ዮሴፍ ማዕከሉ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ አንጋፋ እንደመሆኑ ማደግና ወደ ትልቅ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ጎልቶ መውጣት አለበት ብለዋል።



በ2013 በጀት ዓመት ማዕከሉ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በሀገራችን የቱሪዝም ዘርፍ ላይ ያደረሰውን ተጽዕኖ በማጥናት፤ ይህን ተከትሎም በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የማማከርና የአጭር ጊዜ ስልጠናዎች መሰጠታቸው ተቋሙ ትልቅ አቅም እንዳለው ያሳያል ብለዋል።



# የተግባር ስልጠና



የአንደኛ ዓመት ሰልጣኞች በተለያዩ የቱሪስት መዳረሻ-ዎችና ሆቴሎች ላይ ትምህርታዊ ጉብኝት አደረጉ፡፡

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ነሐሴ 22/2013 ዓ.ም

የአንደኛ ዓመት ሰልጣኞች በክፍል ውስጥ በንድፈ ሃሳብ የተማሩትን በተግባር ለማየት ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን በጠበቁ ሆቴሎችና ሎጆች እንዲሁም በቱሪስት መስህብ ስፍራዎች ላይ ትምህርታዊ ጉብኝት አድርጓል፡፡



የትምህርታዊ ጉብኝቱ ከተደረገባቸው ስፍራዎች መካከል በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ ሙዚዬሞች፣ጢያ መካነ ቅርስ፣አዳዲ ማሪያም፣አንድነት ፓርክና ቢሾፍቱ ውስጥ የሚገኙ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎችና ሎጆች ይገኙ-በታል፡፡




የትምህትርታዊ ጉብኝቱ በክፍል ውስጥ በንድፈ ሃሳብ የተማሩትን ለመረዳት እንደሚያስችላቸው መምህር ፍሬው አበበ ገልጸዋል፡፡

የአስተዳደርና ልማት ዲን አቶ ዳንኤል በቀለ በበኩላቸው የማሰልጠኛ ማዕከሉ ለዘርፉ እያበረከተ ያለውን አስተዋ-ጽኦ ገልጸው የሰልጣኞች የተግባር ስልጠና የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ በእቅድና በጀት ተደገፎ የሚሰራ የተቋሙ መለያ ነው ብለዋዋል ፡፡



ጉብኝቱ ላይ የተሳተፉት ሰልጣኞችም ትምህርታዊ ጉዞ በማድረግ በተግባር የተደገፈ ስልጠና ማግኘታቸው የሀገ-ራችንን የቱሪዝም ሀብት በማወቅ ለማስተዋወቅና እንግ-ዶችን በአግባቡ ተቀብለው ለማስተናገድ በአጠቃላይ ወደ ስራ ዓለም በሚቀላቀሉበት ወቅት ብቁ አገልግሎት ለመስጠት ያስችለናል ብለዋል፡፡





# የማሰልጠኛ ማዕከሉ አፈጻጸም ግምገማ መድረክ



**አንጋፋው የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሠልጠኛ ማዕከል የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸምና የ2014 ዓመት ዕቅድ ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት እካሄደ።**

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ነሐሴ 15/2013 ዓ.ም

በኢትዮጵያ የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ባለሙያዎችን በማፍራት ላለፉት አምስት አስርት ዓመታት የኢንዱስትሪው የጀርባ አጥንት የሆነው የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል በ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክ-ክር አድርጓል።

ማዕከሉ ባሳለፍነው አመት ያከናወነውን ተግባር አስመልክቶ የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ አስቴር ዳዊት አቅርበዋል። በተለይም ከማስተማሩ ጎን ለጎን አጫጭር ስልጠናዎች፣ምርምርና የማማከር ሥራዎችና ተያያዥ ዘርፈ ብዙ ተግባራቱ በባለድርሻ የውይይቱ ተሳታፊዎች አድናቆት ተችሮታል።

የኮቪድ 19 ወረርሺኝን ተከትሎ እንደ ሀገር ኢንዱስትሪው የገጠ-መውን ፈተና ለመወጣት በርካታ ሙያዊ ሥራዎችም ተሰርተዋል። ሪፖርቱን ያቀረቡት የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር "የኮሮና ተፅእኖ እንደ ሀገር ያደረሰውን ተፅእኖ ተቋሙ በጥናትና ምርምር ዘርፍ የሰራው ሰፊ ጥናትና ጥናቱን ተከትሎ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለሚገኙ በዘርፉ ለተሰማሩ ድርጅቶች እስከ ታች በመ-ውረድ የተሰራው የማማከር አገልግሎት የ2013 በጀት ዓመት ስኬታማ ሥራ እንደሆነ ገልፀዋል።"

የህዝብ እንደራሴው ምክር ቤት የሴቶች ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ አባላትም ዘርፉ በቅንጅት እየሰራው ያለው ስራ የሚ-መሰገን መኾኑንና ማሰልጠኛ ማዕከሉ የሰራቸው ተግባራት የሚደ-ነቁ እንደሆነ ተናግረዋል።

በጉባኤው ላይ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ በተቋሙ የዕቅድና በጀት ክትትል ዳይሬክተር አቶ ኃይሉ ነገዎ የቀረቡ ሲኾን የባህልና ቱሪ-ዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም ዘርፍ ሚኒስተር ዴኤታ በክብርት ወይዘሮ ቡዜና አልቀድር አወያይነት ግብአትና አስተያየት ተሰጥ-ቶበታል።

ከዚሀ በተጨማሪም የተቋሙ የሪፎርም ጥናት ሰነድም የመዋቅር ጥናቱ አባል በሆኑት በመምህር ዓብይ ከበደ ቀሮቦ ውይይት ተደርጎበታል።





# አረንጓዴ አሻራ



የማሰልጠኛ ማዕከሉ ሰራተኞችና የስራ ኃላፊዎች የችግኝ ተከላ መርሃግብር አካሄዱ፡፡

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ሐምሌ 29/2013 ዓ.ም

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ሰራተኞችና የስራ ኃላፊዎች ከአስር ሺህ በላይ ሀገር በቀል ችግኞችን ተክለዋል፡፡

የማዕከሉ ማህበረሰብ የችግኝ ተከላ ያካሄዱበት በወንጪ ሀይቅ፣ በፖርቹጋል ድልድይ እና በደብረብርሃን የልቼ ስምምነት በተካሄደበት ታሪካዊና የቱሪስት መስህብ በሆኑት ቦታዎች ላይ ነው፡፡

የችግኝ ተከላ መርሃግብር ከተከናወነባቸው ቦታዎች መካ-ከል በፖርቹጋል ድልድልይ ተገኝተው መርሃግብሩን ያስጀመሩት የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት በቱሪስት መስህቦች ላይ የተተከሉ ችግኞችን ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በመሆን በመንከባከብ እንዲጸድቁ ይደረጋል ብለዋል፡፡ በመስህቦቹ አካባቢ ለሚገኙ ወጣቶች የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎችና የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎቶችን ለመስጠት እቅድ መያዙን ጨምረው ገልጸዋል፡፡

የግራር ጃርሶ ወረዳ አስተዳደር ምክትል ኃላፊ አቶ አብዮት ግርማ በበኩላቸው ታሪካዊውን የፖርቹጋል ድልድይ አካባቢ ከሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ጋር ማልማት እንደጀመርን ማህበረሰቡን የሚጠቅሙ ጉዳዮች ላይ በጠንካራ ትስስር እንደምንሰራ ተስፋ አለኝ ብለዋል፡፡




የማሰልጠኛ ማዕከሉና ገነት ሆቴል ሰራተኞች እና አመራሮች ከ853 ሺህ ብር በላይ ለሀገር መከላከያ ሰራዊት ድጋፍ ማድረጋቸው ተገለጸ፡፡

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ነሀሴ 13 /2014 ዓ.ም

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል በወቅ-ታዊና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማበርከት የተቋሙ ሰራተኞች የስራ ኃላፊዎች ከ353 ሺህ ብር በላይ ድጋፍ ማድረጋቸውን የአስ-ተዳደርና ልማት ዲን አቶ ዳንኤል በቀለ ገለጹ፡፡

ከማዕከሉ ሰራተኞች በተጨማሪ ገነት ሆቴል 500 ሺህ ብር የለገሰ ሲሆን በድምሩ ከ853 ሺህ ብር በላይ የሀገራችንን ሉአላዊነት ለማስከበር በጦር ግንባር እየተፋለመ ለሚገኘው የሀገር መከላከያ ሠራዊት በመለገስ ያላቸውን አጋርነት አሳይተዋል ብለዋል፡፡

ከገንዘብ ልገሳ በተጨማሪም የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴርና ተጠሪው ተቋማት የተሳተፉበት የደረቅ ስንቅ ዝግጅትና የደም ልገሳ መርሃ ግብር መካሄዱ ይታወሳል፡፡



